**ኣድሚንስትራቲቭ ሜዲካል ኦፊስ ኣሲስታንት - ጆን ማርሻል ህንጻ** *ቅድመ ሁኔታ*; ሳይንስ ወይም ሂሳብ ጥምር ክሬዲት; ነጻ የቴክ ዝግጅት ኮሌጅ ክሬዲት; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ; ተጨማሪ ክፍያ***

ኣድሚንስትራቲቭ ሜዲካል ኦፊስ ኣሲስታንት (AMOA) ከምንጊዜውም በላይ በማደግ ላይ ያለ ለበሽተኞች እንክብካቤ እና ስኬታማ የሆነ የሓኪም ቤት ጽ/ቤት፣ የጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታል ውስጥ በተባባሪነት የሚሰራ የጤና ባለሙያ ለመሆን የሚያስችል ኮርስ ነው። እነዚህ ስፔሻሊስቶች ተባባሪ የጤና ባለሙያዎችን የሚከተሉትን በመሙላት ማለትም ኣስፈላጊ የጸሃፊ ስራ፣ በሽተኛ መቀበል፣ በኮምፒተር መዝገቦች መሰነድ እና የሓኪም ቤት ጽ/ቤት መሳሪያዎች መጠቀም የመሳሰለውን ስራ በመስራት ይረዳሉ:: ተያይዞ የሚሰጠውን የጤና ስልጠና ካጠናቀቁ በኋላ ለወደፊቱ ቋሚነት ያለውን ስራ ወዲያው ሊያገኙ ይችላሉ::

**የኤሮስፔስ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ማኑፋክቸሪንግ ሬንየር ቢች ሃይ ስኩል** *ቅድመ ሁኔታ የለውም; ሂሳብ ጥምር ክሬዲት;ነጻ የቴክ ዝግጅት ኮሌጅ ክሬዲት; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ሲያትል በኣለም ትልቁ የኣውሮፕላን ካምፓኒ እና ተባባሪ ፋብሪካዎች ማእከል ናት። ሞያችሁን እና የኮሌጅ ተቀባይነታችሁን ኣውሮፕላን እንዴት ማገጣጠም፣ መጠገን እና ማሻሻል እንደሚቻል መማር ይጀምሩ። የስራ ደህንነት፣ መሳሪያዎችን መለየት እና ባግባቡ መጠቀም፣ በፍጥነት ማገጣጠም፣ ብረት እና ኣሉሚኒየም መብሳት እና ከቅልቅል ብረት የተሰሩ ብረቶች ኣውሮፕላን ምርት ላይ እንዴት ኣንደሚያገልግሉ ተማራላችሁ። በተጨማሪ በሙያው የስራ ልምድ እና የኮሌጅ ክሬድት ታገኛላችሁ።

**ኣውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ – ቦታው የሚወሰን ይሆናል** *ቅድመ ሁኔታ የለውም; ጥምር ክሬዲት;ነጻ የቴክ ዝግጅት ኮሌጅ ክሬዲት; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ኣስፍቶ ማሰብን እና የመኪና ኢንዳስቱሪ ላይ ከፍተኛ ፍላጎት የሚጠይቅ ተግባር ላይ የተመርኮሰ ትምህርት መማር ትፈልጋላችሁ? የኣውቶሞቲቭ ኢንዳስትሪ ጠንካራ መሰረትና ስራ የሚያስገኝ ጥበብ ትማራላቹህ። ስለ ፍሬን፣ ጠቅላላ ጥገና እና ባጠቃላል የመኪና ስርዓት ኣንዴት እንደሚሰራ ትማራላችሁ። ሙያው የሚጠይቀውን መመዘኛ የሚያሟላ ሰርቲፊኬት ታገኛላችሁ። በተጨማሪም የኮሌጅ ክሬዲት ታገኙበታላችሁ።

**ኮንስትራክሽን ትሬድ – ሬኔር ቢች ሃይስኩል** *ቅድመ ሁኔታ የለውም; ጥምር ክሬዲት የለውም; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ይህ ፕሮግራም የህንጻ ስራ ልምድ ክፍል ውስጥ በሚሰጥ እና በተግባር ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እንደ ቤት ለሌላቸው ትንንሽ ቤቶችን መስራት ላይ ልምድ የሚሰጥ ነው። የሚሰጡ ስልጥናዎች እንደ ኣናጺነት፣ የውሃ መስመር፣ ኤሌክትሪሻን፣ ቀለም ቀቢነት እና ሌሎችም ያጠቃልላል። ትምህርቱ ስለ ሁሉም የህንጻ ግንባታ ደረጃዎች ከመሰረት እስከ ጣራ ያጠቃልላል። ኮርሱ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች በቅድመ አፕረንትሽፕ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ዕ ድል ያገኛሉ::. ሃይ ስኩል ከጨረሱ ቡኋላ ተማሪዎች በቀጥታ የስራ ልምምድ (ኣፓረንቲስሽፕ) እድል ያገኛሉ።

**የባልትና ትምህርት (የምግብ ኣሰራር) – ሬኔር ቢች ሃይስኩል** *ቅድመ ሁኔታ *; ጥምር ክሬዲት የለውም; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ; ተጨማሪ ክፍያ***

የሆቴል እና ባልትና ኣገልግሎት በሲያትል በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ ካሉ ሞያዎች ኣንዱ ነው። ኣስደሳቹን እና ጥረት የሚጠይቀውን ሞያዊ የባልትና ትምህርት ወስዳችሁ ባለሙያ ሼፍ፣ የኬተሪንግ ኣገልግሎት፣ ምግብ ቤት፣ የዳቦ ጋገራ እና የምግብ ኣገልግሎት ባለሙያ ይሁኑ ። ከፍተኛው ስልጠና ምግብ ማዘጋጀት፣ የምግብ ጥበብ እና ምግብ ማቅረብ፣ የምግብ ኣያያዝ ጥንቃቄ፣ ጽዳት፣ ስራ መተካት፣ባጠቃላይ ኮርሱ ለተለያዩ የሙያ ችሎታዎች እንደ ኬተሪንግ እና ለከፍተኛ ተመሳሳይ ትምህርት ያዘጋጃል።

**የዲጂታል ኣኒሜሽን እና ጌም ዲሳይን – AIE / ኤ.አይ.ኢ. በሲያትል ማዕከል** *ቅድመ ሁኔታ *; ስነ ጥበብ ጥምር ክሬዲት; ኮሌጅ ክሬዲት; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ኣኒሜሽን እና ጌሞችን መፍጠር! የ2 ዲ አኒሜሽን እና የ3ዲ ጽንሰ ሃሳብ ንድፍና ስቶሪ ቦርዲንግ ይማሩ: ለአኒሜሽንና ጌም እንዱስትሪ ሙያዎች አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን ይማሩ::. የኣካዳሚ ኦፍ ኢንተራክቲቭ ኢንተርቴንመንት (AIE) በኮምፒተር ጌም ዴቬሎፐመንት እና የስሪዲ ኣኒሜሽን ዲጂታል ሜዲያ ዘርፍ ዋና መሪ ነው። ይህ ኮሌጅ የስሪዲ ኣኒሜሽን፣ የጌም ዲሳይን እና የቪዠዋል FX ትምህርትን በቀደምትነት ይሰጣል። ይህ ኮርስ ለኮሌጅ እና ሙያ ለመዘጋጀት የሚረዳ ጥሩ መዘጋጃ ኮርስ ነው።

**ዲጂታል ኣኒሜሽን: ጌም ፕሮግራሚንግ – AIE / ኤ.አይ.ኢ. በሲያትል ማዕከል** *ቅድመ ሁኔታ *; ሂሳብ ጥምር ክሬዲት; ኮሌጅ ክሬዲት; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ይህ ኮርስ ቪዲዮ ጌሞችን ለመስራት በሶፍት ዌር : በሃርድ ዌር እና በሂሳብ ስሌቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል! ይህ ኮርስ ቪዲዮ ጌሞችን ለመስራት በሶፍት ዌር : በሃርድ ዌር እና በሂሳብ ስሌቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል! ተማሪዎች እንደ ስፔሻላይዝድ የጌም ፕሮግራሚንግ እና የኮምፒዉተር ግራፊክስ እውቀት ዲቭሎፐር ለመስራት የሚያስችላቸውን እውቀት ይማራሉ:: እንዲሁም ተማሪዎች የአልጀብራን : የጂኦሜትሪን: እና የትሪግኖሜትሪን ጽንሰ ሃሳብ: ከኮምፒዉተር አፕልኬሽን ጋር በማገናኘት ይማራሉ:: ይህ ኮርስ አዲስ ወይም ለምድ ያላቸውን ፕሮግራመሮች ያገለግላል:: የኣካዳሚ ኦፍ ኢንተራክቲቭ ኢንተርቴንመንት (AIE) በኮምፒተር ጌም ዴቬሎፐመንት እና የስሪዲ ኣኒሜሽን ዲጂታል ሜዲያ ዘርፍ ዋና መሪ ነው።

**የ እሳት አደጋ መከላከልና ድንገተኛ የህክምና አገልግሎት – ሬኔር ቢች ሃይስኩል** *ቅድመ ሁኔታ የለውም; ጥምር ክሬዲት የለውም; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ይህ ኮርስ ተማሪዎችን ለእሳት ኣደጋ እና ለሌሎች ኣደጋዎችን መከላከል ስራ ያዘጋጃል። እጩው ለመምራት፣ እራሱን እና ሌሎችን ማስተዳደር፣ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን እና በዓላትን ጥሩ ሁኔታ እንዲፈጠር በጥንቃቄ ለማካሄድ ይችላል።; የመምራት ብቃቱን በጋሃዱ ዓለም፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ እና የንግድ ተቋማት/ስራ ላይ ተግባር ላይ ማዋል ይችላል። እና እንዲሁም ከሌሎች ጋር በተለያዩ የት/ር ዕሶች ላይ ስልጠናዎችን በማጠናቀቅና ለከፍተኛ ደረጃ ለመዘጋጀት አብሮ የመስራት ችሎታቸውን ለመመዘን::

**የጤና ሳይንስ/ የህክምና ረዳት (ሜዲካል ኣሲስታንት) – -ጆን ማርሻል ህንጻ** *ቅድመ ሁኔታ*; ሳይንስ ወይም ሂሳብ ጥምር ክሬዲት; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ; ተጨማሪ ክፍያ***

ተለማማጅ የጤና ረዳት መማር በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ ያለው የኣላይድ ሄልዝ እና የሄልዝ ሳይንስ ሞያ ኣካል ነው። ተማሪዎች የሓኪሞች እና የሌሎች የህክምና ባለሙያዎች ቃላት እና የሜዲካል ኣሲስታንት እና የጤና ጥበቃ ሞያ ይማራሉ። ፕሮግራሙ ብሔራዊ HOSA የተማሪዎች መሪነት ፕሮጀክት፣ ኮርሶች፤ ኮምፒተር ፕሮግራሞች፣ የኢንዳስቱሪ ስታንዳርድ፣ የኮሌጅ ትምህርት ኣና የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በትምህርት ቤት እና ስራ ላይ ይማራሉ።

**የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ: ኮምፒውተር ኔትዎርኪንግ – ሬኔር ቢች ሃይስኩል** *ቅድመ ሁኔታ የለውም;; ጥምር ክሬዲት የለውም; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

በሃይስኩል እያሉ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አድቫንስድ ክላስ መውሰድ ይፈልጋሉ? ለኮሌጅ የሚከፍሉበትን መንገድ ወይም የአይ. ቲ ሙያ መጀመር ይፈልጋሉ? የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ኮርሶችና በሲስኮ CCNA እና የማይክሮሶፍት ቴክኖሎጂ አሶሲየት (MTA) ወደ እንዱስትሪ ሰርተፊኬሽን ያደርሳሉ:: ይህ ለወደፊቱ ከፍተኛ እርምጃ ነው:: የኮምፒዉተር ሃርድዌር: ሶፍትዌር እና ኔትዎርኪንግ ኦፕሬቲንግ ሲስተም ይማሩ:: የኢንዱስትሪ ሰርተፊኬሽንና የኮሌጅ ክሬዲት ያግኙ::

**የማሪታይም ኦፐረሽን /የባህር ሳይንስ /: ትርንስፖርትና ሎጂስቲክስ - የሲያትል ማሪታይም አካዳሚ - ባላርድ** *ቅድመ ሁኔታ የለውም;; ጥምር ክሬዲት የለውም; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

በፔጀት ሳዉንድ ውስጥ በመርከብ ላይ እንዴት እንደሚሰሩ ይማሩ! ይህ ኮርስ ዘመናዊውንና ባህላዊውን የባህር ላይ እና የቀዘፋ ክህሎቶችን ከኢንጂን እድሳትና ጥገና ስልጠና ጋር በማጣመር ይሰጣል::በዓሳ ማጥመጃ ጀልባዎች : በፌሪ ጀልባዎች: በጭነት መርከቦችና በሌሎችም እንዴት መስራት እንደሚቻል ይማራሉ! በማሰስ: በማሰር: በማዕበል: በጀልባ አያያዝ: በቁልፎች: በድህንነት: በመገናኛ: በራዳር: በሜትሮሎጂ: በመሳሪያዎች አጠቃቀም: እና የማሪን ኢንጂን እድሳትና ጥገና ላይ መሰረታዊ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ:: ከሃይስኩል በኋላ የወደብ ጥበቃ ሰርተፊኬት ሊያስገኝልዎት ለሚችለው የበጋ ስራና ለተጨማሪ ስልጠና ይዘጋጁ::

**የባህር ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ማኑፋክቸሪንግ – ሬኔር ቢች ሃይስኩል** *ቅድመ ሁኔታ የለውም; ሂሳብ ጥምር ክሬዲት;; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ሲያትል በዉሃና በማሪትይም ኢንዱስትሪ ውስጥ በማኑፋክቸሪንግ የተከበበች ናት:: ለኮሌጅና ለማሪትይም ማኑፋክቸሪነ ሙያዎች እራስዎን ያዘጋጁ:: እዚህ ኮርስ ላይ በመሳተፍ የስራ ደህንነት፣ መሳሪያዎችን መለየት እና ኣጠቃቀም፣ መገጣጠሚያዎችን ማገናኘት፣ ኣሉሚኒየም እና ቲታኒየም መብሳት፣ የማሪታይ ኢንዳስቱሪ ላይ የሚያገልግሉ የተቀላቀሉ ብረቶች ኣጠቃቀም እና ጠቃሚ የኮሌጅ እና የሙያ ችሎታዎችን ትቀስማላችሁ። ጂኦግራፊ፣ የካርታ ችሎታ እና የባህር ጎዞ የዚህ ኮርስ ኣስፈላጊ ኣካላት ናቸው።

**ሚዲያ አርት: ቪዲዮ ፕሮዳክሽን - ቦታው የሚወሰን ይሆናል::** *ቅድመ ሁኔታ የለውም; ስነ ጥበብ ጥምር ክሬዲት*

በዚህ ኮርስ ተማሪዎች መጠነ ሰፊ የሆኑ የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ክህሎትና የራሳቸውን የሚዲያ አርት ፖርትፎሊዮ ማዘጋጀት ይጀምራሉ:: ተማሪዎች የፕሮዳክሽንን ሶስት ደረጃዎች ይማራሉ እንዲሁም የፕሮዳክሽን ስራዎች እንደ ኤዲቲንግ: ስክሪፕት መጻፍ: ዲዛይን ማዘጋጀት: መብራት: የካሜራ ስራ: የድምጽ ፕሮዳክሽን: ዳይሬክቲንግ: እና ግራፊክ ዲዛይንን ይማራሉ::

**የነርስ ረዳት – ዌስት ሲያትል ሃይስኩል** *ቅድመ ሁኔታ*; ሳይንስ ጥምር ክሬዲት; ነጻ የቴክ ዝግጅት ኮሌጅ ክሬዲት; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ; ተጨማሪ ክፍያ***

የነርስ ረዳት (ነርሲግ ኣሲስታንት) ትምህርት ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቡኋላ ለሚሰጥ የሄልዝ ሳይንስ እና ሌሎች ተመሳሳይ የነርስነት ሞያዎች ያስገኛል። በተጨማሪም በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ ባለው የነርስነት ሞያ ስራ ያስገኛል። ነርስነት ወደ ሕክምና ሞያ መግቢያ ነው። ተማሪዎች 11 ብሔራዊ የጤና ስታንዳርዶች እንደ የመጀመሪያ እርዳታ፣ በሽተኛ መንከባከብ እና እናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ የመሳሰሉ ምእራፎች ላይ ይማራሉ። ተማሪዎች መጀመሪያ መሰረታዊ እውቀት እና ችሎታ ክፍል ውስጥ እና ሓኪም ቤቶች ውስጥ ይፈተናሉ ቀጥሎ የስቴት ላይሰንስ ለመውሰድ ፈተና ይወስዳሉ። ክፍል ውስጥ የሚሰጠው ኮርስ ብሔራዊ HOSA ኣስተዳደር፣ ችግሮች መፍታት እና የሕክምና ልምድ በመስጠት እድሎችን ይከፍታል ::

**የማስተማር አካዳሚ/የትምህርት ሙያዎች - ሳውዝ ሌክ ሃይስኩል** *ቅድመ ሁኔታ የለውም;; ጥምር ክሬዲት የለውም; የኢንዱስትሪ ማረጋገጫ*

ይህ አጠቃላይ ኮርስ ዓለምን እና የማስተማር ስራንና የትምህርት ሙያን ለማሰስ የሚረዳ መንገድ ነው:: ይህን በመማር ኮርሱ በተለያዩ የት/ቦታዎች ከ2ኛ ደረጃ በኋላ ባሉት የማስተማር ፕሮግራሞች ዉጤታማ ለመሆን እና ለወደፊቱ በጣም ተፈላጊ ወደ ሆነው ሙያ ለመድረስ የሚያስችል ልምድና እድል የሚሰጥ ነው:: ወደሚከተሉት የሙያ እድሎች ሊያደርስ ይችላል:: እንርሱም: የአጸደ ህጻናት: ረዳት አስተማሪ: መምህር: ር/መምህር: እና የት/ቤት ካውንስለር ናቸው::